
ספריית פיג'מה לקטנטנים

**ለቤተሰባዊ ተሳትፎ የሚመከሩ**

ታዳጊ ሕጻናት ከወንድና ሴት ጓደኞቻቸው ጋር መሆን ይወዳሉ። አብረው አንዳንድ ጊዜም ተለያይተው መጫወት ይችላሉ፤ ተመልሰውም አብረው ጓደኛ ይሆናሉ። በእያንዳንዱና በእያንዳንዷ ውስጥ ተመሳሳይና ልዩ የሆኑትን ለመለየት የሚማሩት በዚህ መንገድ ነው።

**ፊታቸው እኩል እንዳልሆነ ሁሉ አስተሳሰባቸውም እኩል አይሆንም።**

(እንደ ባቢሎናዊው ታልሙድ)




የQR ትርጉም እና በላዩ ላይ ይፃፉ - አማር / Pyc / Eng

**ውይይት - በጋራና በተናጠል**

ጋሊና ጋያ ነገሮችን አንድ ላይ ማድረግ ይወዳሉ፤ ግን ደግሞ በተናጠል፦ መወያየትና ማወቅ ትችላላችሁ፦ ታዳጊ ሕጻናት ከወንድም፣ ከሕብረተሰቡ ወይም ከእናንተው ከወላጆች ጋር ምን ማድረግ ይወዳሉ? ብቻቸውንስ ምን ማድረግ ይወዳሉ?

**ጋሊና ጋያ ሊጎበኙ ይመጣሉ**

ከጋሊና ጋያ ጋር መጫወትና ታሪኩን መተወን ይፈልጋሉ? የQR ኮዱን ስካን ያድርጉና ሁለት የሚያማምሩ ዳክዬዎችን ፕሪንት በማድረግ ቆርጠው በማውጣት ታሪኩን ከእነርሱ ጋር መተወን ይችላሉ...!

## እንስሳትና ስዕላዊ መግለጫዎች

በግ፣ እንቁራሪት ወይስ ቢራቢሮ? - ምስሎቹን አንድ ላይ ማየትና የተለያዩ እንስሳትን ማግኘት ይገባል። በስዕሉ ውስጥ ያለውን የእንስሳት ድምጽ ማሰማት ወይም እንደርሱ መንቀሳቀስ ይችላሉ፦ እንደ ቢራቢሮ መብረር፣ እንደ ንብ ጥዝዝ ማለት ወይም ... ሌላ እንደ ማን?

## ተከተለኝ! - የእንቅስቃሴ ጨዋታ

እንደ ጋሊና ጋያ አብረው መራመድ ይችላሉ፦ በቤት ውስጥ መንገድ ማዘጋጀትና በገመድ ወይም በተለያዩ ነገሮች ምልክት በማድረግ በአንድ አምድ ውስጥ መሄድ ይችላሉ - አንዱ ከሌላው በኋላ ወይም ምናልባትም አንድ ላይ ጎን ለጎን። መሪው "ተከተሉኝ!" ብሎ በጠራ ቁጥር መቀያየርም ደግሞ ይቻላል።